# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 8 ቁጥር 2 የካቲት 23 ቀን 2013 ዓ.ም.


## ኢትዮጵያ-አድዋ-ምኒልክ አንድም ሦስትም ናቸው

*የአድዋ ድል 125ኛ ዓመት መታሰቢያ ምክንያት በማድረግ የድምጽ ቅጂውን ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ*

https://www.youtube.com/watch?v=AS-0PTNqau8&pbjreload=101

ያ ትውልድ ተቋም ለ125ኛው የአድዋ ክብረ በዓል እንኳን አደረሳችሁ እንላለን። አድዋን ስናከብር ኢትዮጵያን እናስባለን፣ ጀግኖቻችንን እንዘክራለን፣ ኢትዮጵያዊነትን ከፍ እናደርጋለን፣ ሰንደቅ ዓላማችንን እናውለበልባለን። ወረራና ዝርፊያ አስከፊነቱን ትውልድ ይማርበት ዘንድ አድዋ ትምህርት ቤት ናት። አድዋ ቤተ መዘክር፣ አድዋ ልቅሶ ናት፣ አድዋ ዕልልታ ናት፣ አድዋ ፉከራ ናት፣ አድዋ ክብር ናት፣ አድዋ ማንነታችን ናት።

አድዋ የኢትዮጵያ፣ አድዋ የአፍሪካ፣ አድዋ የጥቁር ህዝብ ታሪክ ነው። በዕለተ ጊዮርጊስ የካቲት ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ስምንት ሀገር ወራሪ ጦር በምሥራቅ አፍሪካ አከርካሪው የተመታበት ዕለት። የዓለም ድሀ ሀገሮችን የናቀና ጦር መሣሪያውን የተማመነ ኃይል በጋሻ ጎራዴ የተንበረከከበት፣ የነፃነት ጮራ ከወደ ምሥራቅ አፍሪካ የፈነጠቀበት፣ ታሪካዊ የድል ቀን አድዋ! ትናገር አድዋ! ትመስክር አድዋ!

በ1882 ዓ.ም. ጥቅምት ወር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው የነገሱት የኃይለመለኮት ልጅ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በአድዋ ጦርነት የኢትዮጵያን ስም በዓለም ያስጠሩ ጀግና መሪ ነበሩ። ምኒልክ ንግሥናቸውን እንዳገኙ የመጀመሪያው የውጭ ጉዳይ ውል ከኢጣልያ ጋር የተደረገው ነበር። ይህም የስምምነት ውል "የውጫሌው ውል" በመባል ይታወቃል።

የውጫሌ ውል አንቀጽ አሥራ ሰባት የጣሊያንኛው ትርጉም፡- *"ኢትዮጵያ ከአውሮጳ መንግሥታት ጋር ማድረግ የምትፈልገውን ግንኙነት በኢጣሊያ መንግስት በኩል ማድረግ አለባት"* ሲል፤ አማርኛው ደግሞ *"ኢትዮጵያ ከአውሮጳ መንግሥታት ጋር ማድረግ የምትፈልገውን ግንኙነት በኢጣሊያ መንግሥት በኩል ማድረግ ትችላለች"* ይላል።

የአማርኛው የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና ልዕልና ሲያስከብር በተቃራኒው የጣሊያንኛው ትርጓሜ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና ልዕልና መድፈር ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ክብሯንና ጥቅሟን ይነካል።

የዳግማዊ ምኒልክ አርቆ የማሰብ ችሎታ ኢትዮጵያ በኢጣሊያ መንግሥት ቁጥጥር ስር እንዳትገባ ጥረት በማድረግ ነፃነታቸውን ጠብቀው ከሌሎች ሀገራት ጋር ግንኙነትንና ምክር መቀበል ቀጠሉ። በዚህም የተነሳ ኢጣሊያም ኢትዮጵያን ለመያዝ ቁርጥ ሀሳብ አድርጋ በኤርትራ በኩል ትግራይን

መውረር ጀመረች። ምኒልክም ሕዝቡን ለጦርነት ክተት አሉ። ታሪካዊው የአፄ ምኒልክ የክተት አዋጅ ነጋሪት እየተጎሰመ ተላለፈ። በጊዜው እንዲህ ተደምጧል፦

"እግዚአብሔር በቸርነቱ እስካሁን ጠላት አጥፍቶ አገር አስፍቶ አኖረኝ፤ እኔም እስካሁን በእግዚአብሔር ቸርነት ገዛሁ። ከእንግዲህ ብሞትም ሞት የሁሉም ነውና ስለእኔ ሞት አላዝንም። ደግሞ እግዚአብሔር አሳፍሮኝ አያውቅም፤ ወደፊትም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠራጠርም። አሁንም አገር የሚያጠፋ፤ ሃይማኖትን የሚለውጥ፣ በፊት እግዚአብሔር የወሰነልንን ባህር አልፎ መጥቷል። እኔም የአገሬን ከብት ማለቅ፤ የሰውን መድከም አይቼ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር። አሁን ግን በእግዚአብሔር ረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም። የአገሬ ሰው ከአሁን ቀደም የበደልሁህ አይመስለኝም። አንተም እስካሁን አላስቀየምኸኝም። ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ። ጉልበት የሌለህ ለልጅህ፣ ለምሽትህ፣ ለሃይማኖትህ ስትል በሀዘንህ እርዳኝ። ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ። አልምርህም። ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም። ዘመቻዬ በጥቅምት ነውና የሸዋ ሰው እስከ ጥቅምት እኩሌታ ወረይሉ ከተህ ላግኝህ።"

ጣሊያኖች በጄኔራል ባራቲዬሪ የሚመራውን 20 ሺህ ወታደሮቻቸውን ይዘው በ1888 ዓ.ም. የካቲት 23 ቀን አድዋን ወጉ። ከ80 ሺህ እስከ 120 ሺህ የሚገመተው የምኒልክ/የኢትዮጵያ ሠራዊትም በሚገባ ሲዋጋ የሀገሪቱ ተፈጥሮአዊ አቀማመጥና ሀገሬን! ብሎ በቁርጠኝነት ስሜት ቀፎው እንደተነካ ንብ የተነቃነቀው ኃይል የጠላትን ጦር አደናግጦ መግቢያ መውጫ በማሳጣት ቀኑን ሙሉ ጦርነቱ ከተካሄደ በኋላ በሚያስደንቅ አኳኋን ድሉ የኢትዮጵያ ሆነ። ቅኝ አገዛዝ እግሬ አውጪኝ ሲል፤ ነፃነት ከፍ አለ! በምኒልክ መሪነት ሕዝብ ታሪክ ሰራ! ለጥቁር ሕዝብ የነጻነት ተጋድሎ ጮራው ፈነጠቀ። ኢትዮጵያ! በልጆቿዋ ደምና አጥንት ሉዓላዊነቷን አረጋገጠች። በጀግኖቻችን ደም ኢትዮጵያ ክብሯን አገኘች። ልክ የዛሬ 125 ዓመት።

እነሆ ልክ የዛሬ 125 ዓመት በዕለተ ጊዮርጊስ እንደእምነታቸው ታቦቱን ይዘው የተጓዙት ምኒልክ ጠዋት የተጀመረው ጦርነት ረፋዱ ላይ በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት ተጠናቋል። የሰው ቤት ሊያነድ የመጣው ወራሪ፤ ነዶና ዓመድ ሁኖ ተበተነ። ደረቱን አሳብጦ የገባው ሠራዊት፤ አንገቱን አቀርቅሮ ተባረረ። ኢትዮጵያ የሰው ልጅ ለሀገሩ ክብር፣ ለነፃነቱ ጥቁርነቱ ምልክት እንዳልሆነ አሳየች። የአድዋን ድል የዓለም ጥቁር ሕዝቦች ድል እንደሆነ አስመሰከረች። በእናትና አባቶቻችን ክቡር መስዋዕትነትና ተጋድሎ የተገኘው የአድዋ ድል ቅኝ ገዥዎች የነበራቸውን ግፍና ህልም በአጭር ያስቀረ አንጸባራቂ ድል ሆነ።

*__ኢትዮጵያ- አድዋ -ምኒልክ አንድም ሦስትም ሆኑ።__* "ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!" ሲባል አድዋ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያ አድዋ የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች ናቸው። በአድዋ ምድር የደቡብ፣ የምዕራብ፣ የምሥራቅ፣ የሰሜን ወገኖቻችን ደም አለ። አድዋ ኢትዮጵያን የማዳን ዕምብርት ናት፣ አድዋ የጀግኖች መቃብር ናት፣ አድዋ የሰማዕታት ሐውልት ናት፣ አድዋ እምነት ናት፣ አድዋ ጽናት ናት፣ አድዋ ኢትዮጵያዊነት ናት፣ አድዋ ምኒልክ ናት።

የአድዋን ክብረ በዓል ስንዘክር የታሪኩን አስተማሪነትና ኢትዮጵያውያን ለሀገራችን ያለንን ፍቅርና ክብር እየኮራንበት ነው። አድዋ በምኒልክ የክተት አዋጅ ውስጥ መተባበርን፣ እምነትን፣ መስዋዕትነትን፣ ፍቅርን ያስተምረናል። አድዋ በሰው ልጆች ዘንድ ብቀላና ቂም በቀል እንዳይኖር በጣልያን ምርኮኞችና በአስተዋይ መሪው ምኒልክ ይቅር ባይ ውሳኔ ያመላክተናል። አድዋ ለሀገር አንድነትና ነፃነት የሚፈስ ደም ክቡር መሆኑን በጀግኖቻችን ውስጥ ያሳየናል። አድዋ ወረራ፣ ጦርነት፣ ትዕቢት መጨረሻው ውርደት መሆኑን ይተርክልናል። አድዋ የሰው ልጅ በሰውነቱ እኩል መሆኑን፣ ክብሩን ፈላጊ፣ መብቱን አስከባሪ ለመሆኑ ምስክር ነው።

**ባንቺ ነው አድዋ**

የሦስት ሺህ ዘመን ታሪክ አስከብረሽ
የኢትዮጵያን ሰንደቅ የጥቁር ህዝብ አርገሽ
በቅኝ መገዛትን ያስቀረሽ በነበር
ብሄራዊ ስሜት ጎልቶ በሀገር ፍቅር
ጀግንነት በጎራው ሲያቅራራ ሲጨፍር
ሽለላ ሲታወድ በጀግና ሲፎከር
ጋሻና ጎራዴ ሁነው በአንድነት
የጠላትን አንገት ቀልተው ሲጥሉት
መብረቁ ሠራዊት ሆኖ ነጎድጓድ
የጠላትን ምሽግ ሰባብሮ ሲንድ
በኢትዮጵያዊነት የበለው ቀረርቶ
የጠላትን ሠራዊት ትጥቁን አስፈትቶ
እጁን ተራስ አርጎ፤ ጠላት ሲማረክ
ከጀግና ሥር ወድቆ፤ ሊማር ሲምበረከክ
ዛሬ ታሪክ ሁኖ በትውልድ፤
ለትውልድ ሲተረክ
የድል "ምሥራች" ተሰማ
ተውለበለበ ሰንደቅ ዓላማ
ከተራራው ጫፍ ከማማ
በኢትዮጵያዊነት ዜማ
ለጥቁሮች የነፃነት ደስታ
ድምጽ አሰማ እምቢልታ
ነጋሪት ተደለቀ! አስተጋባ እልልታ
ቀኝ ገዢውን ያን ወራሪ
መቃብር ከተሽ ታሪክ ሰሪ
ያንቺ ነው አድዋ ሁሌም ተከበሪ።

ጋሻ ሲመክት፣ መድፍ ሲያጓራ
ጎራዴ ሲቀላ፣ ጀግና ሲያቅራራ
የጎበዝ እናት ስትል በለው! በለው!
ጥማቱን ከባ በውሃ ስትቆላው
በዕለተ ጊዮርጊስ ሲታይ መንፈስ ቅዱስ
ወርሃ የካቲት መሀሌት ሲቆሙ ለሀገር ሲቀደስ
ምድረ ወራሪ መፈጠር ሲጠላ
ኢትዮጵያ ልጅሽ ላንቺ ሲል ሲቀላ
አንድነትን ወልደሽ ሀገርን ያስከበርሽ
ህይወትን ገብረሽ ህይወትን የዘራሽ
አድዋ የምዬ ዘላለም ያኑርሽ።

ድንቅነሽ ከአብራክሽ፤ ተገኝታ ያኮራችሽ
የተፈጥሮ ጸጋሽ ሕይወት የዘራብሽ
አህዋፍ ከሰማይ ዝማሬ ሚደምቁት
አራዊት በአንድነት ውሃሽን ሚጋሩት
ሣርሽን ሚግጡ፣ ቅጠል ሚበጥሱት
ወንዞች ተራሮችሽ ውበቱን የሰጡሽ
ባንቺ ነው አድዋ ሁሌም እናከብርሽ።

ወልቃይት ጠገሌ በሰሊጥ ተውባ
ከፋና ኢሉባቡር የቡና አበባ
ማንጎ የወሊጋ
የሐረሩ ሰንጋ
ጽንሰ ወርቅ ያዶላ
አክሱም ላሊበላ
የአፋር ሀገር ፍቅር
የባሌ ሶፎመር
የጎጃም ማኛ ጤፍ
የንቦች ዝማሬ አንቺ የማር ሰፈፍ
የጎንደር እስክስታ
የጋምቤላ እቢልታ
የኦሮሞ ረገዳ፣ ከበሮ በትግሬ

በጎጃም መሲንቆ፣ ክራር በጎንደሬ
የወሎ ክምክም
ተከቦ ከረኩም
የጉራጌ ጭፈራ የሸዋ ሽበላ
ባህል ተወራራሽ ሀገር እንዳትላላ
ጉራማይሌ ቋንቋ፣ ምልአተ ዘር
በኢትዮጵያዊነት እንዲተሳሰር
ያገርሬ ሰው ባዋጅ ከፍሎ መስዋዕት
ኢትዮጵያችን ብለን ያለነው ባንድነት
ባንቺ ነው አድዋ ሁሉም ይወቁት።

እዮሃ አበባዬ፤ ቃና የልጆችሽ
አበባዮዎሽ፤ ለምለም እንቁጣጣሽ
መስቀሉ አበባ እሳት የደመራ
የነብዩ ልጆች ድምቀተ ዝየራ
የጌታ ልደቱ
የመውሊድ ብስራቱ
ዮህንስ ጥምቀቱ
ፋሲካ ስቅለቱ
ትንሳዔ ሰልስቱ
ሲበላ ሲጠጣ፤ ሀገር መደሰቱ
ባንቺ ነው አደዋ እርካታ መስጠቱ።

አድዋ ሰምና ወርቅ
ጦርም ነሽ ፍቅር
አድዋ ጀግንነት
ድል፣ ህይወት፣ ነጻነት
ይቅር ባይ አንድነት
ተጫዋች ምርኮኛ
ያለሃሳብ ያስተኛ
ዓለም የገረመው
ዛሬም የሚያከብረው
አዛኝ በምህረቱ
አማኝ በታቦቱ
እምዬ ምኒልክ የጥቁሮች አባት
እቴጌ ጣይቱ ምስጢረ ብልሃት
ሁሌም የሚነሱት
ባንቺ ነው አድዋ ዘላለም ኩሪበት።

ከደምም ደም አለ ያውም የጥቁር
የጀግና አጥንት ቅስት የሆነሽ ማገር
በብልህ እንስቶች ጥንስስ ተዋህደሽ
በሰንደቅ ዓላማ ፈክተሽ አሸብርቀሽ
ከበሮ ጽናጽል ተዋህዶ ድምጽሽ
ትንፋሽሽን ሰተሽ ህይወትን ያተረፍሽ
አድዋ! ባንቺ ነው ኢ...ት..ዮ..ጵ...ያ..ን ያኖርሽ።
አድዋ! ባንቺ ነው ትውልድ ይዘክርሽ።
አድዋ! ባንቺ ነው ትምህርት ትሆኛለሽ።
አድዋ! ባንቺ ነው ሁሌም ትኖሪያለሽ።
አድዋ! ባንቺ ነው ዘላለም ያኑርሽ።

ክብር ለአድዋ ጀግኖች!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!
የያ ትውልድ ታሪክ ህያው ነው!!!

የካቲት 23 ቀን 2013 ዓ.ም. (March 02, 2021)

## ያ ትውልድ ተቋም

ስልክ፦ 7033004302
ድረ ገጽ፡ www.yatewlid.org, www.yatewlid.com
ኢሜል፡ yatewlid@gmail.com
ምሥለ ገጽ፡
https://www.facebook.com/yatewlid.thegeneration